# እናስበው

የፍቅርን ሁሉ መጨረሻ
የመሥዋዕትነትን መዳረሻ
የግለኝነትን ማብቂያ
የትንቢት ቃሉን ማጽደቂያ
አየነው . . . በመከራው በሕመሙ
በስጋውና በደሙ . . .
በስቃይና በእንግልቱ
በስቅላቱና በሞቱ
አየነው . . .
ለሰው ልጅ ኃጢአት ተሰዶ
ከአምላክነቱ ተዋርዶ
የሥጋን መከራ ሲቀበል
ከእናቱ እይታ ሲነጠል
አየነው . . .
እኛስ?
ከፍቅሩና ከመሥዋዕትነቱ
ከትሕትናውና ከትዕግሥቱ
በትንሹ ጨልፈናል?
ከጽናቱ ተምረናል?
ሌላው ቢቀር . . .
በዛሬው ቀን፣ በዚህች ሰዐት መከራውን አስበናል?
አልዋሽም . . .
አላሰብኩም።
ታድለዋል የሚያስቡ
የአምላክን ቃል አክብረው ትእዛዛቱን ያነገቡ
የጾም፣ የስግደት፣ የጸሎትን ክቡር ጸጋ የደረቡ
ለሕማሙ ነቅተው ተግተው ሲያስታውሱት የሚውሉ . . .
ወደ ቤቱ የሚገቡ
ታድለዋል።
እስቲ እኛም እንደነሱ
እንዳይርቅብን መንፈሱ
ለአንዲት ደቂቃ እናስበው
ስለክብሩ እንዘክረው
ምናልባትም . . .
አንድነታችን የላላው፣ ተስፋችን የዳመነው
እምነታችን የደከመው፣ ጥረታችን የመከነው
ችላ ስላልነው ይሆናል . . . ከመሀላችን ስላራቅነው።
ኢትዮጵያ የአምላኳ ናት የፈጣሪነቱ መመስገኛ
የፈሪሀ እግዚአብሔር ምንጭ የግማደ መስቀሉ መገኛ
ስለሆነም . . . እናስበው
ምንጫችንን አናድርቀው።

---

ቴዎድሮስ አበበ
Washington, DC